ያ ትውልድ

*የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን*

ያ ትውልድ ቅጽ 4 ቁጥር 2 *ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም.*

# <u>“የትግሉ ነው ሕይወቴ”</u>

*(የሜይ ዴይ 1966 ዓ.ም. እልቂት 40ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት፣ ለሕዝብ መንግስት፣ ለላብ አደሩ ዓለም አቀፋዊነት ወጣቶች ደማቸውን ያፈሰሱበት ዕለት። ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም.። በበለው፣ በፍለጠው፣ በአሳስቀህ በለው . . . የተዋቀረው የፋሽስታዊ ደርግ አገዛዝ ሕፃናትንና ወጣቶችን በአደባባይ በቢ አር እና በክላሽ እሩምታ የፈጀበት ዕለት። ለላብ አደሩ የጮኹ ሰላማዊ ወጣቶች በጥይት የተቆሉበት ዕለት። በድናቸው ሳይቀር ላባከኑት ጥይት ሁለት መቶ ሃምሳ ብር የተሸጠበት ዕለት። ሜይ ዴይ ዓመጽ አርግዛ ጥይት ያዘነበችበት ዕለት። ልክ የዛሬ 40 ዓመት።

የእነኚያ ሕፃናት የግፍ ጭፍጨፋ ዛሬም ኢትዮጵያን ያስለቅሳታል። ዛሬም አታንሷቸው፣ አትዘክሯቸው፣ አታልቅሱላቸው ባዩ ቢበራከትም ታሪክ ነውና፣ እንደ የካቲት 12ቱ ሰማዕታት የሜይ ዴይ ሰማዕታትም በደርግ የታረዱ ልጆቿ፣ በደርግ የጥይት አካፋ የተጨፈጨፉ ናቸውና ሀገርና ሕዝብ ሰንደቃቸውን ዝቅ አድርገው ይዘክሯቸዋል። ክብር ለእናንተ እንላቸዋለን።

ዓለም አቀፍ የላብ አደሮች ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. በአብዛኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ከዕለቱ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አካባቢ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) መሪነትና በአብራክ ድርጅቱ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ (ኢሕአወሊ) አስተባባሪነት በየአካባቢው በሰላማዊ ሰልፍ ለማክበር ተወሰነ።

ከደርግ አረመኔያዊ ባህሪ አንፃር ሜይ ዴይን በዕለተ ቀኑ ሚያዝያ 23 ማክበር እንደሚያዳግት የተረዳው ኢሕአፓ ለመታሰቢያነት የመረጠው ዕለት አርብ ሚያዝያ 21 የደም ቀን ሆነ። በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከሁለት ሺህ በላይ ወጣቶች በአንድ ቀን በደርግ ፋሽስቶች በየአስፋልቱ ተደፉ። ምድር በደም ታጠበች። በየሆስፒታሉ የወጣቶች አስከሬን እንደ እህል ክምር አስከሬን በአስከሬን ተቆለለ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ በሚያዳግት አካኳን የሰው ልጅ ሰው ላይ ጨከነ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ደም በጠማው የደርግ አረመኔ ወታደሮች ተለቀሙ። እናቶች ለዋይታና ለለቅሶ ተለጉመው ወደ ውስጥ ያለቀሱበት ቀን ቢኖር ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» የዛሬ አምስት ዓመት ሜይ ዴይን አስመልክቶ ለሜይ ዴይ፣ ለቀይ ሽብር፣ ነፃ እርምጃ፣ ቤት ለቤት አሰሳ እና በጥቅሉ በደርግ ትውልድ ማጥፋት ሰለባ ለሆኑ ሰማዕታት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ www.yatewlid.com , www.yatewlid.org ድረ ገጽ ይፋ ማድረጋችን ይታወሳል። በዕለቱ ካቀረብነውን ጋዜጣዊ መግለጫ (ጊዜውን በማስተካከል) ይህንን እንደግመዋለን፦

*“. . . ደርግ ከጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. የመንግሥቱ ኃ/ማርያም በተለይ በኢሕአፓ ጥላ ሥር የተሰለፉ፣ የደገፉ፣ ያዩ፣ ያለፉትን ከሕፃናት እስከ አዛውንት ደም በማፍሰስ የበላይነቱን ለማረጋገጥ፣ ደም የተሞላ ጠርሙስ ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. “በአብዮት” አደባብይ ከሰበረ በኋላ የቀይ ሽብር ድህረ ዝግጅት “ነፃ እርምጃ” የበርካታዎችን ሕይወት በየደቂቃው እየነጠቀ ያለፈበት ፋሽስታዊ ወቅት ነበር።*

*ዓለም አቀፍ የላብ አደሩን ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ከደርግ ልክ ያጣ ጭፍጨፋ አንፃር በዕለቱ ማክበር እንደማይቻል የተገነዘበው ኢሕአፓ፣ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ያለውን ታማኝነትና የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሰልፍ ከድርጅቱ እየከዱ ወደ ደርግ መግባት በጀመሩ አንጃዎች ሙሉ መረጃ ለደርግ በመድረሱ መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ጀሌዎቹ አብዮት አደባባይ በምሳሌነት ያፈሰሱትን ደም ሊጠጡ ቋምጠውና አድፍጠው ተጠባበቁ።*

*ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች “ፍጹም ነው እምነቴ” እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። አዲስ አበባ የደም ዳመና አንዣበበባት። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች ሽብር ሆነ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፣ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፣ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፣ እናቶች አባቶች ሀዘን፣ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው። ልክ የዛሬ 40 ዓመት።*

*አብረን ተሰልፈን፣ አብረን ጮኸን፣ አብረን ታግለን፣ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፣ ልናስባቸው ይገባል። ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱት “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም” “የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም” እየፈከሩ፣ “ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት” እየዘመሩ፣ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፣ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፣ ደማቸው ደማችን ነውና፣ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት በመውሰድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።*

*የዚያን ትውልድ ታሪክ ማሰባሰብና ለታሪክ ተመራማሪዎች፣ ፀሀፊዎችና ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ አንዱ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው የዚያ ትውልድ አካል የዛሬን ቀን በማስታወስ ለሀገራቸው ሉዓላዊነትና ለሕዝባቸው ክብር ሲሉ በተለያዩ አገዛዞች መስዋትነት ለከፈሉና እየከፈሉ ላሉ እንዲሁም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው በትውልድ መመተር ቀይ ሽብርና ነፃ እርምጃ ለወደቁት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ **<u>ያ ትውልድ ድረ ገጽ</u>** (www.yatewlid.org or www.yatewlid.com) ከዛሬ ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 29, 2012) ጀምሮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አበርክተናል።”*

እነሆ! የሰማዕታት ወገኖቻችን መታሰቢያ «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» ዛሬ አምስት ዓመቱ። አረመኔው ደርግ በድናችሁን ለመቃብር ባያበቃውም ሀውልታችሁ ላይ ሊፃፍ የሚገባው ስማችሁና ምስላችሁ በ«ያ ትውልድ ድረ ገጽ» ከፍ ብሏል። ከሀውልታችሁ በላይ ***<u>“ታሪካችሁ ሕያው ነው!!!”</u>*** ሁሌም ይነበባል። «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» በደርግ አገዛዝ ትውልድ መመተር ለተገደሉ ሰማዕታት ወገኖቻችን ሀውልት፣ በሕይወት ላሉ ቤተሰቦቻቸው መዘክራቸው ነው። «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» ማንም ሊያፈናቅለው የማይችል ዘላለማዊ ሀውልት። «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» ስማችሁ ከመቃብር በላይ ከፍ ይል፣ የመረጃ ምንጭ ትሆኑ ዘንድ የተተከለ ***<u>“የትውልድ ሀውልት”</u>*** ። ጀግንነታችሁ በታሪክ

ማህደርነት ለዘላለም ይቀመጥ ዘንዳ፣ ምን ሰርተው አለፉ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንዳ እነሆ! «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» አምስት ዓመት ጉንጉን አበባ አሳቅፎ፣ የእናት ሀገራችሁን ሰንደቅ ዓላማ አልብሶ በየቀኑ እንድትታወሱ ከፍ ከፍ እንዳደረግናችሁ ሁሉ የምናደርገው ጥረት ይበልጥ እንደሚጠናከር በዚህ አጋጣሚ ቃል ልንገባ እንወዳለን።

ያፈሰሳችሁት ደም፣ የከሰከሳችሁት አጥንት እኛን ለዚህ አብቅቶን በእናንተ ደም ህውልታችሁ ተጽፏል። በእናንተ አጥንት ድረ ገጻችሁ ተገንብቷል። የአቅማችንንና የችሎታችንን እስካበረከትን ድረስ የጎሊና እርካታው አብሮን አለና ሁልጊዜም አብረናችሁ ነን። በስማችሁ የቆመው «ያ ትውልድ ድረ ገጽ» ነገ የሀገርና የትውልድ አኩሪ ሀብት ለመሆኑ ጥርጣሬ አይገባንም። ሀውልታችሁ፤ ነገ ሀገር የናንተ ስትሆን ለምርምር፣ ለጥናት፣ ለማስተማሪያ ይፈለጋልና የዚያ ጊዜ ***"የትግሉ ነው ሕይወቴ"*** ዝማሬአችሁ የእናንተ ትንሳዔ ይሆናል። "ቢወቀጥ አጥንቴ፤ ቢንቆረቆር ደሜ" ዝማሬአችሁ እውነትም ሀገር ያለመልማል።

«ያ ትውልድ ተቋም» በፋሺስት ደርግ ጭፍን ጭፍጨፋ ለተዳረጉ ወገኖቻችን ያለንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን በዛሬው ዕትማችን በ500 ሺህ ከሚገመቱ የቀይ ሽብር ሰማዕታት መካከል አንድ ጠብታ መታሰቢያነቱን ከአንድ ቤተሰብ ለተገደሉ ወገኖች አድርገናል። በድረ ገጽ ማህደራችን ካካተትነው የ23 ቤተሰቦች ውስጥ የተገደሉትን ስም ዝርዝርና ምስል ፎቶአቸውን የያዘውን ሀውልታችሁን ብቅ አድርገናል።

ደርግ እናትና አባትን ገድሎ ማንነታቸውን ሳያውቁ እንዲያድጉ የተገደዱ የትላንት ሕፃናት የዛሬ ጎልማሶች/ኮረዳዎች ቀላል አይደሉም። ደርግ ልጆቻቸውን በመላ ገድሎ "ምን ትሆናላችሁ?" ቀረርቶውን የዘፈነ ጨካኝ የሚል ቃል የማይገልጸው ዘመነ መቅሰፍት ነበር። ከፋሺስት ጣሊያን ቀጥሎ ሬሳ አንስቶ የረሸነ አገዛዝ ቢኖር ደርግ ነው። ደርግ ወንድምን ከወንድም፣ እህትን ከእህት፣ ወንድምና እህትን፣ እናትና ልጅን፣ አባትና ልጅን፣ አባትና እናትን እያጣመረ የፈጀ፤ ሲገድል ጀምሮ ሲገድል የጨረሰ ኢትዮጵያንና ትውልዱን ዛሬ ለደረሱበት አሳሳቢ አደጋ ከፍተኛውን አስተዋጽዎ ያበረከተ አገዛዝ ነበር።

ለጆሮ ሚሰቀጥጥ፣ ሊታመን የማይችል የጭካኔ ዓይነቶች ማህደር ቢኖር አንዱ ደርግ ነው። እንደ ጰላጦስ በውሃ ሳይሆን እንደ "ጀግንነት" በደም የታጠቡ የደርግ እጆች ዛሬም ጎሊና የሌለው የግፍ ብዕራቸው እያባነነ እንቅልፍ የሚነሳቸውን ድርጊታቸውን "ትክክለኛ እርምጃ" እንደነበር ሊሰብኩ፣ ሊያስተማምኑ ወይም መካዱም ሲያርበተብታቸው አንብበናል፣ ሰምተናል። ዛሬ "ድንጋይ በቅል እየተሰበረ" ነውና የወንጀላቸው መሸሸጊያ ዳግም ፖለቲካው ሲሆን አይ ድፍረት፣ አይ ጎሊና ማጣት ያሰኛል።

| ከአንድ ቤተሰብ በደርግ ቀይ ሽብር ከተገደሉ ውስጥ | | | |
|---|---|---|---|
| ተራ ቁ | ስም ከነአባት | መኖሪያ | መግለጫ |
| 1 | ዓለማየሁ ገብረሃና | ከ 1 ቀ 5 ቤት ቁ 444 | |
| | ፍቅረማርያም ገብረሃና | | |
| 2 | ንጉሱ ከተማ | ከ 1 ቀ 8 ቤት ቁ 1300 | |
| | ኑኑ ከተማ | | |
| | ጌቱ ከተማ | | |
| | ካሱ ተሰማ | | |
| 3 | አሰፋ አወቀ | ከ1 ቀ 6 ቤት ቁ 270 | |
| | ምስጋናው አወቀ | | |
| 4 | ፍትህሽዋ እዝቅያስ | ከ1 ቀ 7 ቤት ቁ 464 | |
| | ይትባረክ እዝቅያስ | | |
| 5 | ብርሃኑ ከበደ | ከ 3 ቀ 34 ቤት ቁ 518/20 | |
| | ፋሲል ከበደ | | |
| 6 | ፊጠነ እሸቱ | ከ3 ቀ 44 ቤት ቁ 1017 | |
| | ግርማ እሸቱ | | |
| | ጌታቸው እሸቱ | | |
| 7 | አለዊ አክሊሉ | ከ5 ቀ 23 | |
| | መሐሙ አክሊሉ | | |
| 8 | አሰፋ ሀጎስ | ከ12 ቀ 11 ቤት ቁ 734 | |
| | ገብረተንሳይ ሀጎስ | | |
| 9 | ወንድወሰን ተፈራ | ከ12 ቀ 19 ቤት ቁ 321 | |
| | ተፈራ የኋላሸት | | |
| | ጀማነሽ ወዳጆ | | |
| 10 | ቲቶ ሀሩይ | ከ11 ቀ 14 | የኢሕአወሊ አመራር አባላት |
| | አክሊሉ ሀሩይ | | |
| | ፍቅሩ ሀሩይ | | |
| 11 | ደምሴ ብርሃኑ | ከ15 ቀ 23 ቤት ቁ 122 | በአንድ ምሽት ሜይ ዴይ 1969 የተገደሉ |
| | ግርማ ብርሃኑ | | |
| | ሞገስ ብርሃኑ | | |
| | ተፈራ ብርሃኑ | | |
| | ተስፋዬ መኮንን | | |
| 12 | ዮሴፍ አዳነ | ከ15 ቀ 28 | ከኢሕአፓ መሥራች አባላት |
| | ቢንያም አዳነ | | በረሃ ላይ የተሰዋ ከኢሕአፓ መሥራች አባላት |
| 13 | አመነው ነገደ | ከ15 ቀ 32 | |
| | ገረመው ነገደ | | ደብዛው የጠፋ |
| 14 | ኃይሉ ደመቀ | ከ15 ቀ 33 | በወር ልዩነት በመንገድ ላይ የተጣሉ |
| | ግርማ ደመቀ | | |
| 15 | ሀጎስ መሐመድ | ከ15 ቀ 34 | |
| | መኮንን ልሳነወርቅ | | |
| | ሽመልስ ኃይሌ | | |
| 16 | መስፍን አሰፋ | ከ21 ቀ 31 | ደብዛው የጠፋ |
| | ሳሙኤል አሰፋ | | ደርግ በመግለጫ የረሸነው |
| 17 | ዓለማየሁ ለማ | | |
| | ስመኝ ለማ | | |
| 18 | ዓለማየሁ ተፈራ | | |
| | አያቁም ተፈራ | | |
| | መኮንን ተፈራ | | |
| 19 | አለምሰገድ አምባው | | |
| | አዛነው አምባው | | |
| | ነጋ አምባው | | |
| 20 | እንግዳወርቅ ከበደ | | |
| | ንጉሤ ከበደ | | |
| | የግልወርቅ ከበደ | | |
| 21 | ትዕግሥት ናደው | | |
| | ቆንጂት ናደው | | |
| 22 | እስክንድር ዓለማየሁ | ሐረር ቀበሌ 8 | |
| | ኃይሌ ዓለማየሁ | ከ24 ቀ 13 | |
| 23 | ወ/ሮ ፀሐይ በለው | ሐረር | እናትና ልጅ |
| | ጥዑም ልሳን | | |

## ከአንድ ቤተሰብ በደርግ ቀይ ሽብር ከተገደሉ ውስጥ ምስላቸው የተካተተ




































**ክብር ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ!!!**
**የሜይ ዴይና የቀይሽብር ሰማዕታት ሁሌም ይዘከሩ!!!**

**«ያ ትውልድ ተቋም»**

**ሚያዝያ** 23 **ቀን** 2009 **ዓ.ም**. (May 01, 2017)
**ድረ ገጽ ፦** www.yatewlid.com, www.yatewlid.org
**ኢሜል ፦** yatewlid@gmail.com, yatewlid@yahoo.com
**ምስለ ገጽ ፦** YaTewlid